*የሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ጽ/ቤት በአሜሪካ፣*
***The Office of His Eminence Archbishop Zena Markos in the USA***
***940 26th Ave. S., Seattle, Washington  98144***
***(206) 720-0827*** (206) 322-3268

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን።**

**በሲያትልና በአካባቢው፥በሀገር ውስጥና በዓለም ዙሪያ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፥ቸርቱ የማያልቅበት ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ፥እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ በሰላም አሸጋገራችሁ። አዲሱንም ዘመን ዘመነ ሉቃስን የሰላም፥የፍቅርና የአንድነት ዘመን እንዲያደርግልን የአምላካችን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን።**

## <u>የተወደደችው የጌታ ዓመት፣</u>

**ከአዝማናት መካከል የተወደደችው የጌታ ዓመት የትኛዪቱ ናት?ስለዚች ስለተወደደችው ዓመት ከመናገራችን በፊት፥ በአጠቃላይ፥ስለዘመናት ትንሽ መናገር መልካም ነው። አዝማናትን ያስገኘ፥የአዝማናት ባለቤት፥አዝማናትን አሳልፎ የሚኖር፥ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ ለዘመኑ ጥንት፥ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም። እግዚአብሔር ከዘመናትና ከአዝማናት በፊት ነበረ። በዘመናትና በአዝማናት መካከልም የወደደውን እያደረገ አለ። ወደፊትም ዘመናትን አሳልፎ፥ያለምንም እንከን ለዘላለም ይኖራል። ስለሆነም ቅዱሳን መላእክት በምስጋናቸው እንዲህ እያሉ ያወድሱታል። «እንስሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠው፥ከዘላለም እስከዘላለም በሕይወት ለሚኖረው፥ለእርሱ ክብርና ውዳሴ፥ምስጋናም በሰጡት ጊዜ፥ሐያ አራቱ ሊቃናት በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ከዘላለም እስከዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ፥ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፥ስለፈቃድህም ሁነዋልና፥ተፈጥረውማል፥ክብር፥ውዳሴ፥ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ፥በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።»ራእይ** 4፥9-11

**ቅዱስ ዳዊትም እንዲህ ብሎአል፥- «አንተሰ አንተ ክመ፥ ወዓመቲከኒ ዘኢየኃልቅ፥ አንተ ግን ያው አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።» ብሎአል። መዝ** 102፥28

**እንግዲህ ይህ በዘመን የማይወሰን ልዑል እግዚአብሔር፥ ዘማናትን እንዴት እንዳስገኘ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ይገልጣል።**

**«እግዚአብሔርም አለ፥ ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ፥ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፤ ለምልክቶች፥ ለዘመኖች፥ ለዕለታት፥ ለዓመታትም ይሁኑ። በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ፥ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁኑ። እንዲሁም ሆነ።» ይላል። ዘፍጥረት** 1፥14

**ቤተ ክርስቲያናችንም በዚህ ቃል መሠረት፥ ዘመናትን ዓመታትን፥ ሱባዔያትን ትቆጥራለች። የቤተ ክርስቲያናችን የቀመሮቿ ሁሉ መሠረት፥ ይህ ቃል ነው። እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዘመን አቆጣጠር፥ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ፥ ዘመን ሲቆጠር፥ እነሆ ዘንድሮ ሰባት ሽህ አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ዓመተ ዓለም ሆነ። ቤተ ክርስቲያን የዘመን አቆጣጠር ስልትዋን፥ በሦስት ዓይነት አገላለጥ ከፍላ ትቀምራለች። ይኸውም፣**

1. **ከዕለተ ፍጥረት እስከ ዕለተ ምጽአት ያለውን መላውን ዘመን፥ዓመተ ዓለም ትለዋለች።**
2. **ከሰው ውድቀት እስከ ክርስቶስ ልደት ያለውን ዘመን፥ አምስት ሽህ አምስት መቶ ዓመተ**

ፍዳ፥ዓመተ ኩነኔ፥ዘመነ ብሉይ፥ ብሉይ ኪዳን፥ትለዋለች።

3. ከክርስቶስ ልደት፥እስከ ዕለተ ምጽአት ያለውን ዘመን፥ ዘመነ ሥጋዌ፥ ዘመነ ሐዲስ፥ ሐዲስ ኪዳን፥ ዓመተ ምሕረት ትለዋለች። በግልጥ አነጋገር፥ዓመተ ዓለም፥ዘመነ ብሉይ ዘመነ ሐዲስ፥ ማለት ነው።

ከዚህ ውስጥ፥ የተወደደች የተባለችው የጌታ ዓመት የትኛዪቱ ናት? የተወደደች ስለ ተባለችው፥ ስለ ጌታ ዓመት፥ የብሉይ ኪዳን አበው፥ በተስፋ ሲጠብቋት፥ ሱባዔ ሲቆጥሩላት፥ ነቢያትም በልዩ ልዩ አገላለጥ፥ ትንቢት ሲናገሩላት ኑረዋል። ለምሳሌ፥ ዳዊት እንዲህ ብሎአል።

«ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር፥ ንትፌሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ። እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት። ሐሜትን እናድርግ፣ በእርስዋም ደስ ይበለን።» ይላል። መዝሙር 117፥24

ኢሳይያስም፥- «በተወደደ ጊዜ ሰምቼሃለሁ፥ በመድኃኒትም ቀን ረድቼሃለሁ፥ እጠብቅህም አለሁ። ምድርንም ታቀና ዘንድ፣ ውድማ የሆኑትንም ርስቶች ታወርስ ዘንድ፣ የተጋዙትንም ውጡ፥ በጨለማ የተቀመጡትን ተገለጡ፤ ትል ዘንድ፣ ቃል ኪዳን አድርጌ ለሕዝቡ ሰጥቸሃለሁ።» ይላል ኢሳ 49፥8

ኤርምያስም፥- «እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር፥ አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል። ይላል ጌታ»........ ከዚያ ወራት በኋላ፥ ከእሥራኤል ቤት ጋራ የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና፥ ይላል ጌታ፣ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። እኔም አምላክ እሆንላቸዋለሁ፥ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑልኛል።» ኤርምያስ 31፥31

ይህንም የኤርምያስን ቃል፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥ ብሉይ ኪዳን ተሽሮ፥ ሐዲስ ኪዳን ለመምጣቱ፥ በዕብራውያን መልእክቱ በምዕራፍ 8 ላይ ምስክር አድርጎ፥ ጠቅሶታል። ዳዊት እግዚአብሔር የሠራት ቀን ብሎ የጠራት፥ ኢሳይያስ የተወደደ ሰዓት፥ የመዳን ቀን ያላት፥ ኤርምያስ ሐዲስ ኪዳን፥ የሐዲስ ኪዳን ወራት፥ ብሎ የተነበያት፥ ይህችን የተወደደችውን የጌታን ዓመት ነው።

## ለመሆኑ፥የጌታ ዓመት የትኛዪቱ ናት?

የተወደደች የተባለችው የጌታ ዓመት፥ አምስት ሺህ አምስት መቶ፥ የመከራና የስቃይ፥ የፍዳና የኩነኔ፥ የፍርድና የመርገም ዓመት ሲፈጸም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነባት ዓመት፥ ዓመተ ሥጋዌ፥ ዘመነ ሥጋዌ፥ ዓመተ ምሕረት፥ የተባለችው ናት። ሰው በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ስለታረቀባት፥ ዓመተ ምሕረት ተብላለች። ሮሜ 5፥10። በኃጢአት ያረጀው፥ የሰው ሕይወት፥ ስለታደሰባት፥ ዘመነ ሐዲስ ተብላለች። ዕብ 8፥1-13። ስለሰው ልጆች ኃጢአት፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ስለፈሰሰባት፥ ሐዲስ ኪዳን ተብላለች።ማቴ 26፥28።

የተወደደች በተባለችው በጌታ ዓመት፥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሁኖ፥ ሥጋ ለብሶ፥ በተገለጠ ጊዜ፥ በተለይ በመምህርነቱ ወራት፥ ያከናወነው መንፈሳዊ አላማውና ተግባሩ፥ በሉቃስ ወንጌል ተብራርቶ ተገልጦአል። ቃሉም እንዲህ ይላል። «ወደ አደገበቱም ወደ ናዝሬት መጣ፣ እንደልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ፣ ሊያነብም ተነሣ። የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ፥ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፣ ለታሠሩትም መፈታትን፥ ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ፥ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል። ተብሎ የተጻፈበትን ሥፍራ አገኘ። መጽሐፉን ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና ተቀመጠ፣ በምኩራብም የነበሩት ሁሉ፥ ትኩር ብለው ይመለከቱት ነበር። ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ ይላቸው ጀመር።» ሉቃስ 4፥16-21። በዚህ በሉቃስ ወንጌል ላይ እንደሰማነው፥ የተወደደች በተባለችው በጌታ ዓመት፣ ለድሆች ወንጌል ተሰብኮላቸዋል፣ በኃጢአት ማሠሪያ የታሠሩትም ተፈትተዋል። ዕውሮችም አይተዋል፣ በዲያብሎስ የተጠቁትም ነጻ ወጥተዋል። ጌታ ሰው የሆነበት ዋና አላማም፥ ይህንና ይህንን የመሰሉትን ተግባራት ለማከናወን ነበር።

<u>አዲስ ዓመት በኢትዮጵያ፤</u>

ከጥንት ከአባቶቻችን ጀምሮ፥ በየዓመቱ ሲደረግ እንደነበረው፥ ይኸውና ዘንድሮም፥ ከመስከረም አንድ ጀምሮ፥ በኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ነው። የጨለማውና የጭፍናው፥ የጉሙና የዝናሙ፣ የወጀቡና የውሽንፍሩ፥ የጎርፉና የማዕበሉ፣ የመብረቁና የነጎድጓዱ፣ የጭቃው፥ የብርዱና የድደኑ፣ የእርሻውና የጉልጓሎው፥ የዘሩና የአረሙ፣ የረኃቡና የችግሩ ባጠቃላይ የመከራው ወራት አልፎ፥ ከመስከረም አንድ ጀምሮ ግን፣ በሰማይ ብሩህ ፀሐይ ይወጣል፣ ተራሮችንም፥ ሰማዩንም፥ ሸፍኖ የነበረው ጉም ይገፈፋል። ብርዱና ድደኑ ይለቅቃል፥ ጭቃውና አሮንቃው ይደርቃል፣ ተራሮች በአደይ አበባ ያሸበርቃሉ። በተስፋ ሲደክሙ የከረሙት ገበሬዎች አዲሱን እህል እሸቱን አሽተው፥ ይቅማሉ፣ የተራቡ ይጠግባሉ፥ ያጡ ያገኛሉ። ስለዚህ መስከረም በኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ አዲስ ዓመት መሆኑ ተገቢ ነው። ይህም በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ወር ከመስከረም አንድ ቀን ጀምሮ የሚታየው አዲስ ነገር ሁሉ፥ የተወደደች የጌታ ዓመት የተባለችው የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ነው። ከመስከረም በፊት የነበረው ሁሉ ደግሞ፥ የብሉይ ኪዳን ምሳሌ ነው። በኢትዮጵያ አዲስ ዓመት በመስከረም፥ አዲስ ነገር እንደሚታይ፥ እንዲሁ በሐዲስ ኪዳንም፥ ሁሉ ነገር በክርስቶስ አዲስ ሁኖአል። ይህንንም በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክቱ እንዲህ ብሎአል። «ወይእዜሰ በክርስቶስ ተሐደሰ ኵሉ ዘኮነ፣ ወኃለፈ ዘትካት፣ ወናሁ ኮነ፥ ሐዲሰ ኵሉ። ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን፥ አዲስ ፍጥረት ነው። አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሁኖአል።» 2ኛ ቆሮ 5፥17።

ሐዲስ ኪዳን ራሱ በሁለት ይከፈላል። አንደኛው ከልደተ ክርስቶስ እስከ ዕለተ ምጽአት ያለው ነው። ሁለተኛው ከዕለተ ምጽአት ጀምሮ ለዘለዓለም የሚሆነው ነው። ከዕለተ ምጽአት በኋላ ስላለው አዲስ ነገርም፥ ክብር ይግባውና መድኃኒታችን በዮሐንስ ራእይ እንዲህ ብሎአል። «ወይቤ ዘይነብር ዲበ መንበሩ፥ ናሁ እገብር ኵሎ ሐዲሰ፥ በዙፋኑም የተቀመጠው፥ እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ።» ራእይ 21፥5።

ዮሐንስም በራእዩ እንዲህ ብሎአል፣ «አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ። ፊተኛው ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባሏ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።» ራእይ 21፥1

<u>ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ፣</u>

ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱን አዲስ ዓመት፥ በወንጌላውያን ስም ትሰይማለች። ይህ የሆነበት ምክንያት፥ ቅድም በሉቃስ ወንጌል እንደተገለጠው፥ ጌታ ሰው የሆነበት አላማ፥ በአርአያነቱና በቤዛነቱ ሥራ፥ ለድኃውና ለችግረኛው ዓለም ወንጌልን ለመስበክ ስለሆነ፥ የሰው ልጆችም፥ ከኃጢአት ማሠሪያ የሚፈቱት በወንጌል ስለሆነ፥ በኃጢአት የታወረው የሰው ልጆች ዓይናቸው የሚበራ በወንጌል ስለሆነ፣ በዲያብሎስ የተጠቁትም የሰው ልጆች ነጻ የሚወጡት በወንጌል ስለሆነ፣ በአጠቃላይ የሰው ልጆች በክርስቶስ አምነው ሊድኑ የሚችሉት፥ ወንጌል ተሰብኮላቸው ስለሆነ፥ ጌታ የአርአያነቱንና የቤዛነቱን ሥራ ፈጽሞ፥ሙቶ፥ ተነሥቶ፥ በክብር ሲያርግ፥ ለድኃው ዓለም ወንጌልን የሚሰብኩ ሐወርያትን ተክቶ ነው።

ከሐዋርያትም መካከል፥ አራቱን ወንጌላት የጻፉ፥ ማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስ፥ ዮሐንስ ናቸው። እነዚህም አራቱ ወንጌላውያን ይባላሉ። እነርሱ በጻፉት ወንጌልም፥ ክርስቶስ በዓለም ተሰበከ። ወደፊትም እስከ ዕለተ ምጽአት ወንጌል በዓለም እንደሚሰበክ፥ ጌታ በማቴዎስ ወንጌል ተናግሮአል።

«ወይሰበክ ዝ ወንጌለ መንግሥት ውስተ ኵሉ ዓለም፥ ከመ ይኩን ስምዓ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ። ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን፥ ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል።» እንዲል፥ ማቴዎስ 24፥14

ሐዋርያትንም ወደ ዓለም የላካቸው፥ወንጌልን እንዲያስተምሩና እንዲሰብኩ ነው። «ወደ ዓለም ሁሉ ሒዱ፥ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፣ ያመነ፥የተጠመቀም ይድናል። ያላመነ ግን

ይፈረድበታል።» ይላል። ማርቆስ 16፥16። በክርስቶስ አምኖ መዳን የሚቻለው፥ወንጌለ መንግሥቱን በመስማት እንደሆነ፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በሏል። «...እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው፣ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።» ሮሜ 10፥14-17። እንግዲህ ክርስቶስን አምነን የምንድንበትን ወንጌል የጻፉልን ወንጌላውያን፥ ማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስ፥ ዮሐንስ፥ ስለሆኑ፥ ይህን ውለታቸውን ለማስታወስ፥ እያንዳንዱን አዲስ ዓመት፥ በየተራ ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ፥ ዘመነ ማርቆስ ወንጌላዊ፥ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ፥ ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ፥ በማለት ቤተ ክርስቲያን ስታስባቸው ትኖራለች። በመሆኑም የዘንድሮው የ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ተረኛ፥ ወንጌላዊ፥ ቅዱስ ሉቃስ ነውና፥ ዘመነ ሉቃስ ይባላል። የያዝነው ዓመት እስኪፈጸም፥ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ እየተባለ ይጠራል። በተጨማሪም ይህ ሉቃስ ወንጌልን ስለጻፈ ሉቃስ ወንጌላዊ ይባላል። ከሰባ ሁለቱ አርድዕት አንዱ ስለሆነ፥ ቅዱስ ሉቃስ  ይባላል።

<u>ቅዱስ የሐንስ፤</u>

ርእሰ ዓውደ ዓመቱ መስከረም አንድ ቀን ብቻ፥ ሁልጊዜ በየዓመቱ ቅዱስ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል። ይህ የሆነበት ምክንያት ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ፥ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን መካከል፥ በብሉይ ኪዳን መጨረሻና በሐዲስ ኪዳን መጀመሪያ ላይ የነበረ ነቢይ ስለሆነ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ በጽንሰም፥ በልደትም፥ በትምህርትም፥ ከጌታ መንፈቅ፥ መንፈቅ ይቀድማል። በመንፈቅ ትምህርቱ፥ ያስተማረውን ትምህርት፥ የሰበከውን ወንጌል፥ የተናረውን ኃይለ ቃል፥ ልደቱን ዕድገቱን፥ በአጠቃላይ የሕይወት ታሪኩን፥ በመጨረሻም፥ ጌታን በዮርዳኖስ እንዳጠመቀና፥ ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ፥ ሄሮድስ እንደገደለው፥ አራቱም ወንጌላውያን ጽፈውለታል። ስለ ታላቅ ሰውነቱም፥ ጌታ እንዲህ ብሎ ተናግሮለታል። «እውነት እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል፥ ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም።»ይላል ማቴ 11፥11። ቀደም ብለን እንደገለጥነው፥ የሀገራችን አዲስ ዓመት፥ የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ በመሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያንም ሁል ጊዜ በየዓመቱ፥ የአዲሱን ዓመት መጀመሪያ፥ ርእሰ አውደ ዓመት ዮሐንስ ብላ፥ የሰየመችበት ምክንያት ታሪኩ ይኸው በዚህ ምክንያት ነው።

የተወደደች የጌታ ዓመት የተባለችው፥ ክርስቶስ ሰው የሆነባት፥ አዲስ ዓመት፥ አዲስ ኪዳን፥ እና የሰው ልጆች የሚያከብሩት አዲስ ዓመት ሲነጻጸር፥ የእኛው ስለሚያረጅ፥ በየዓመቱ ዘመኑ ይለወጣል። መስከረም አንድ ቀን አዲስ ነው ያልነው፥ ነሐሴ መጨረሻ ላይ አሮጌ ይሆናል። በመስከረም አዲስ ፈክተው የነበሩት አበቦች ብዙም ሳይቆዩ ይረግፋሉ። ምሳሌነት ቢኖረውም፥ «እስመ ምሳሌ ይውህድ እምአማን። ምሳሌ ከእውነተኛ ነገር ያንሳል።» እንደተባለ፥ በየዓመቱ፥ ያለፈውን አሮጌ፥ መጭውን አዲስ፥ ማለት ተገቢ ነው።

የተወደደች የተባለችው የጌታ አዲስ ዓመት ግን፥ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ፥ በክርስቶስ ለሚያምኑቱ ለሰው ልጆች ሁሉ፥ ሁል ጊዜ አዲስ እንጅ፥ በየዓመቱ የምታረጅ አዲስ አይደለችም። ሁልጊዜ ንስሐ በሚገባ በሰው ሕይወት ውስጥ አዲስ ነች። ስለዚህ በተወደደችው የጌታ ዓመት፥ በጌታ ዓመት ወንጌል ይሰበካል፤ በጌታ ዓመት ዕውሮች ያያሉ፣ በጌታ ዓመት ደንቆሮች ይሰማሉ፣ በጌታ ዓመት ሐንካሶች ይረታሉ፣ በጌታ ዓመት ጎባጦች ይቀናሉ፣ በጌታ ዓመት ለምጻሞች ይነጻሉ፥ በጌታ ዓመት የተጠቁት ሁሉ በወንጌል ነጻ ይወጣሉ። በጌታ ዓመት የታሠሩት ሁሉ ከማእሠረ ኃጢአት ይፈታሉ።

ታዲያ ይህ ሊሆን የሚችለው፥ ሰው ንሥሐ ገብቶ አዲሱን ዓመት ሲቀበለው ነው። ሰው አዲሱን ሕይወት ክርስቶስን ሲለብሰው ነው። ሰው ሕይወቱን ክርስቶስ የሚመላለስበት በንስሐ የተዘጋጀ፥ ጥርጊያ ጎዳና ሲያደርገው ነው። «የጌታን መንገድ አዘጋጁ፥ ጥርጊያውንም አቅኑ፥ እያለ፥ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምጽ፥ ዐዘቅቱ ሁሉ ይሙላ፥ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይበል፣ ጠማማውም የቀና መንገድ ይሁን፣ ሸካራውም መንገድ ትክክል ይሁን። ሥጋም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ። ተብሎ እንደተጻፈ»። ሉቃስ 3፥6። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፥ የሰው ውሳጣዊ ሕይወት መታደስ እንዳለበት፥ እንዲህ ብሎ ተናግሮአል። «ስለዚህ አንታክትም፥ነገር

ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ፥ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።» ብሏል 2ኛ ቆሮ 4፥16። የሰው ውሳጣዊ ሕይወቱ የማይታደስ ከሆነ ግን፥ አዲሱ ዓመት በተራሮች ላይ አዲስ ነው። በሰው ሕይወት ላይ ግን የማይጠቅም አሮጌ ነው። እያንዳንዱን ቀን፥ እያንዳንዱን ወር፥ እያንዳንዱንም ዓመት፥ መልካም የሆነውን ሥጋዊውንም ሆነ፥ መንፈሳዊውን ሥራ ካልሠራንበት፥ አሮጌ ነው። ከሠራንበት ግን አዲስ ነው። ምክንያቱም የመዳን ቀን ዛሬ ነውና፥ የመታደስም ቀን ዛሬ ነውና፥ በንስሐ የመለወጥ ቀንም ዛሬ ነውና። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የኢሳይያስን ትንቢት ጠቅሶ፥ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ተርጉሞ በጻፈው መልእክቱ እንዲህ ብሏል። «እነሆ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው። እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው።» 2ኛ ቆሮ 6፥2።

<u>*የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ሆይ !*</u>

እነሆ ዘመኑ ተለወጠ፥ እነሆ ዘመኑ አዲስ ሆነ፣ የሰው ሕይወትሳ ተለውጧል ወይ? የሰው አካሄዱስ ታድሷል ወይ? በሰው ሕይወት ውስጥ የጥንቱ ኢትዮጵያዊው ሥነ ምግባር፥ ፍሬ አፍርቷል ወይ? እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለዚህ ጥያቄ መልስ ይፈልጋል።

ልዑል እግዚአብሔር አዲሱን ዓመት ይባርክልን !!!
ወንጌል የሚሰበክበት፥ችግረኞች የሚረዱበት፣ የተራቡ የሚጠግቡበት፥ዓመት ያድርግልን።
እሥረኞች የሚፈቱበት፥ዕውሮች የሚያዩበት፥ዓመት ያድርግልን።
በተለይም የተጠቁ ነጻ የሚወጡበት ዓመት ያድርግልን።
በልዩ ልይ ምክንያት የቆሰለው የሰው ልብ የሚፈወስበት ዓመት ያድርግልን።
የእግዚአብሔር ጸጋ ፍቅር የሚበዛበት፥ ሰላም በዓለም የሚሰፍንበት ዓመት ያድርግልን።
በተለይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ችግርዋ የሚወገድበት፥ በረከትን ከእግዚአብሔር የምታገኝበት ዓመት ያድርግልን።
ይህችን ያለንባትን ሀገር አሜሪካንም የሰላም ሀገር ያድርግልን! አሜን።

አባ ዜና ማርቆስ ሊቀ ጳጳስ፤